# ሸሪፍ አባ ጃርሶ ወጣቱ አርበኛ

የተወለደው በወለጋ ክፍለሃገር በነቀምት ከተማ ነው።የመለስተኛ ገበሬ ልጅ ሲሆን እሱም በእርሻው ዙሪያ ዕድሜው በሚፈቅድለት ተግባሮች ፣በማረም፣ወንጭፍ ይዞ ሰብሉን ከጅንጀሮና ከአእዋፍ በመጠበቅና በእረኝነት ስራ ተሰልፎ ለቤተሰቡ የድርሻውን ያበረክታል።የበኸር ልጅ በመሆኑ አባቱ የሚተማመኑበትና የሚኮሩበት ልጅ ነው።

እሱ በተወለደበትና ባደገበት አካባቢ እንዲህ እንደአሁኑ የዘመናዊ ትምህርት ዕድል አልነበረም። ህብረተሰቡ ለትምህርት የነበረው ግምትና ግንዛቤ አነስተኛ ቢሆንም የሸሪፍ አባት ልጃቸው ፊደል እንዲለይ የነበራቸው ፍላጎት ከፍተኛ ነበር።በዚህም በከባቢያቸው በሚገኘው ደብር ውስጥ ፊደል ያስቆጥሩ የነበሩ ካህን በመኖራቸው ልጃቸው ሸሪፍ በካህኑ ደጃፍ ከሌሎች ጥቂት የእድሜ አጋሮቹ ጋር ፊደል እንዲቆጥር ወስነው አስጀመሩት።ሸሪፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሃሁ ወደአቡጊዳ መልእክተና ከዛም ወደዳዊት ተሸጋገረ፤በሰፈሩ ድንቅ ጉድ ተባለ። የሰፈርተኛው ደብዳቤ ጸሃፊና አንባቢ ለመሆን በቃ።በዚያን ጊዜ ትንሽ ፊደል የለየ ለመንግስት አነስተኛ ያስተዳደር ስራዎች የሚፈለግበት ወቅት ነበር።ወጣቱ ሸሪፍ ግን ከአስር ብር ለማይበልጥ ደመወዝ ተቀጥሮ ከመስራት የያዘውን የቤተሰብ የእርሻ ስራ መርጦ የወደፊቱን ኑሮ በተስፋ እያለመ በዚያው በተወለደበት ቀዬ ዕድሉ የሰጠውን ተቀብሎ ለመኖር ወሰነ።

ይህ ተስፋውና ፍላጎቱ  እውን ሳይሆን፣ገና በጧቱ የአስራሁለት ዓመት ልጅ እንደሆነ ሌላ አቅጣጫ ያዘ።

በዚህ ዕድሜው ነበር ጠላት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር ተንቀሳቅሳ ብዙ የአገራችንን መሬት፣ገጠርና ከተማ በቁጥጥሯ ስር ለማድረግ የበቃችው።በዚህ የጠላት ወረራ ያልተደሰቱትና የአገራቸውን መወረር ከተቃወሙት መካከል የሸሪፍ አባት አባ ጃርሶ አንዱ ናቸው።መቃወም ብቻ ሳይሆን በከባቢው ጫካ ገብተው ከጠላት ጦር ጋር ግብግብ የገጠሙ አርበኞች በመኖራቸው እራሳቸውን ለአገራቸው ነጻነትና ክብር አሳልፈው ለመስጠት በመወሰን ተቀላቀሉ።

የአምስት ልጆች አባት የሆኑት አባ ጃርሶ ቤቴን ልጄን፣ንብረቴን ሳይሉ፣እንደአንዳንዶቹ የጠላት ሰበካና ቅስቀሳ ሳይገዛቸው እምቢ ላገሬ ብለው፣ቤት ትዳር፣ደስታ፣የሚኖረው አገር ሲኖር ነው ብለው ቤተሰባቸውን ላልጠነከረው ለበኸር ልጃቸው ለሸሪፍ አደራ ሰጥተው ጦራቸውን ወልውለውና ስለው ጋሻቸውን ወድረው ጫካ ገብተው ከአርበኞች ጋር ተቀላቀሉ።

ቤተሰባቸው ለንግድ ስራ ወደ ሌላ ቦታ እንደሄዱ አሶራ።አባ ጃርሶ ግን አልፎ አልፎ ጨለማ ለብሰው ብቅ በማለት የቤተሰባቸውን ሁኔታ እየተከታተሉና እያበረታቱ የጠላትን እንቅስቃሴ እየጠየቁ መረጃ ሰብስበው ይመለሱ ነበር። ከቀን ወደቀን የጣሊያኖቹ ቁጥጥር እየከፋ ሲመጣ የአባ ጃርሶም እግር እየራቀ ሄደ።

ከከባዊው በመራቃቸው የቅርብ ዘመድም ደጋግሞ በመጠየቁ ጥርጣሬ እንዳይፈጠር በማለት ለንግድ በሄዱበት አገር በድንገት ታመው አረፉ የሚል መርዶ ቤተሰቡ ፈጠረና ለሃዘን ተቀመጠ።በዚህ መልክ ሊነሳ የሚችለውን ጥርጣሬና አደጋ በብልሃት ቤተሰቡ አሶገደ።

ወጣቱ ሸሪፍ የሙት ልጅ፣ህጻናት ወንድምና እህቶቹን የሚያሳድግ የቲም ተባለና ሁሉም የሚያዝንለት ሆነ።ከባቢውን ለመቆጣጠር አንድ የጣሊያን ጦር ሰፈር በመቋቋሙ ሸሪፍ ሌላ የገቢ ምንጭ ለመፍጠር እረዳው። የእንቁላል ነጋዴ ሆነና ከጣሊያን ወታደሮች ጋር ለመቀራረብ እረዳው።ይህ የንግድ ስራ በገቢውም ብቻ ሳይሆን ጫካ ለገቡት አባቱና ለቀሩት አርበኞች የዜና ምንጭ ሆኖ የውስጥ አርበኝነት ስራ ለመስራትና አርበኞቹን ከጠላት ጭፍጨፋ ለመታደግ እረድቶታል።ቀስ በቀስ በሚሰጠው አገልግሎትና በሚያሳየው ትህትና የጣሊያኖቹን

ቀልብ ለመሳብ ችሎ በበር እንቁላል ከማቀበል አልፎ እቤት ውስጥ ለመግባት ለመውጣት የሚያስችል አመኔታን አገኘ። የሚሰጠው አገልግሎት ከእንቁላል አድራሽ ወደ ቤት ተላላኪነት ጩሎነት ተቀየረ። ይህም በቅርበት የጣሊያኖቹን እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለአርበኛ አባቱና መሰሎቻቸው  መረጃ አሳልፎ ለመስጠት ትልቅ ዕድል ከፈተለት።የአርበኞቹ የምስጢር ጓደኛና የውስጥ አርበኛነቱ ታውቆለት የሚገናኘው ሰው ተመድቦለት ነበር።

ጣሊያኖች ሌላውን ሕዝብ ለማታለል በሚጠቀሙበት ዘዴ ማለትም ጣሊያን የአንተን የኦሮሞውን ነጻነትና መብት ለማስከበር የመጣ መንግስት ነው፤ሲጨቁንህ የነበረው የአማራ አገዛዝ እንዲወገድልህ እንጂ አንተን ለመበደል አልመጣንም የሚለውን ባዶ ቅስቀሳና ሰበካ ወጣቱ ሸሪፍ እንዲቀበላቸው ብዙ ቢሞክሩም ሸሪፍን ከእምነቱና አባቱ ከተሰለፉበት ዓላማ ንቅንቅ ሊያደርገው አልቻለም።ለማስመሰል ሲል እየሳቀና እያመሰገነ ስራውን ይሰራ ነበር።

ሸሪፍ የነቃ አእምሮ ስለነበረው የጣሊያኖቹን ቋንቋ በተወሰነ ደረጃ ለመረዳት በቅቶ ነበር።ሲሰክሩ የሚዘላብዱትን ሙሉ ለሙሉም ባይሆን በተወሰነ ደረጃ እየተከታተለ በተለይም ምን እንዳደረጉና ምንስ ለማድረግ እንዳቀዱ የሚያስረዳውን  ምስጢር ለሚገናኘው ያርበኞች መልእክተኛ አሳልፎ በመስጠት ትልቅ ሚና ተጫውቷል።በዚህ ሁኔታ ሸሪፍ ከጣሊያኖቹ ጋር ከሁለት ዓመት በላይ ተቀራርቦ ሰራ።የብዙ ሊሬ ጌታ ሆነ።በሚያገኘው ገንዘብ ተጨማሪ ከብቶችና የእርሻ መሬት እየገዛ የቤተሰቡን ገቢ አሳደገው።ተከታይ ወንድሙም እየጠነከረ ለሸሪፍ አጋርና ተተኪ ሆነለት።

ሁል ጊዜ እንደተመኙትና እንዳሰቡት አይሄድም ፤ከጣሊያኖቹ መካከል አንድ  በጣም ከይሲ የሆነው የሸሪፍን መግባትና መውጣት  ገና ከጅምሩ አልወደደውም ነበርና በጥርጣሬ ዓይን እየተመለከተ ፊት ይነሳው ነበር።ሸሪፍም ያላዬ እየመሰለ የዚህን ዘረኛ አካሄድ በተጠንቀቅ ይከታተል ነበር።የዚህ ሰው አድራጎት ወደባሰ ችግር ሊያመራ እንደሚችል ይገምት ነበር።መገመትም ብቻ አይደለም ችግሩ ቢፈጠር በማለት ብልሃትና ዘዴዎችን ቤተሰቡን በማይጎዳ መልኩ ማዘጋጀት ከጀመረ ውሎ አድሯል።ከቤተሰቡ ጋር እንደማይዋደድ፣ከነሱ ተለይቶ እንደሚኖር፣በእረፍት ጊዜውም አጎቱ ከሚኖርበት አገር ጊምቢ እየሄደ እንደሚያሳልፍና ወደፊትም ወደዚያው የመኖር ፍላጎትና ዓላማ እንዳለው ባዘቦቱ ቀን እየተናገረ ጣሊያኖቹ በእሱና በቤተሰቡ መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት እንዳያዩ የማሳሳትና የማዘናጋት ስራውን በሚገባ አጠናቋል።ቤተሰቡንም በሚገባ አዘጋጅቷል።

የፈሩት ይደርሳል እንደሚሉት የዚያ ከይሲ ጣሊያን ወታደር በደል ገደቡን አለፈና ጎረምሳውን ሸሪፍን ለመምታት እጁን ሰነዘረ።እልህ የተናነቀው የአርበኛው የአባ ጃርሶ ልጅ፤ቀደመና ካላሰበበት ቦታ ላይ ጣሊያኑን እንካ ቅመስ አለው።ያ ይሆናል ብሎ ያልጠበቀው ጣሊያን መሬት ላይ ተዘርሮ ማማማሪያ እያለ አድኑኝ ማለት ጀመረ ፣ወጣቱ ሸሪፍም ማሪያምን ሰማይቤት ፈልጋት እያለ ደጋግሞ ደቆሰውና ሌሎቹ ተሯሩጠው ሊይዙት ሲመጡ እግሬ አውጭኝ ብሎ አመለጠ።ይህ ዕለት ከሚወደው ቤተሰቡና ከሚወዳት አገሩ የተነጠለበት ዕለት ሆነ።

ወጣቱ ሸሪፍ በከባቢው ቢኖር ሊደርስበት የሚችለውን አደጋ በማጤን፣ከአርበኞቹም ጋር ለመቀላቀል እንዳይችል አርበኞቹ ቦታ ቀይረው ስለነበር የነበረው አማራጭ ወደሱዳን መሰደድ ነበር።ከብዙ የእግር ጉዞና ድካም በኋላ በደቡብ ሱዳን ጁባ ከተባለው ከተማ ደረሰ።የስራ ዕድል ባለመኖሩ ጥቂት ሳምንታት ካሳለፈ በኋላ ጉዞውን ወደ ካርቱም ቀጠለ።ካርቱም እንደገባ በአንድ የእንግሊዝ መንግሥት ባለስልጣን በሆነ ግብጻዊ ቤት እንደለመደው በጩሎነት ተቀጥሮ ስራ ጀመረ።መቼም ሲፈጠር የታደለ ነውና አረብኛ ቋንቋውንም፣እንግሊዝኛውንም ለመረዳት ጊዜ አልፈጀበትም።በሚሰጠው አገልግሎት የተደሰተው ግብጻዊ እንደልጁ ቆጥሮት ሾፌሩ

እንዲሆን የመኪና መንዳት ችሎታ እንዲማር አደረገው።በአጭር ጊዜ ውስጥ የተዋጣለት ሾፌር ሆነ።

በዚሁ ስራው ላይ እንዳለ ጣሊያኖች ድል ሆነው ከአገራችን እንደሚወጡና ንጉሰ ነገስቱም ቀዳማዊ ሃይለስላሴ በሱዳን በኩል ወደአገራቸው እንደሚመለሱ ካርቱም በሚገኘው በስደተኛው መድሃኒዓለም ዙሪያ ይነገር ስለነበር ወጣቱ ሸሪፍ ንጉሱን አጅቦ ወደ አገሩ ለመመለስ ያደረበት ፍላጎት በልዩልዩ ምክንያቶች ሳይሳካለት ቀረ።አገሩ ለመግባት ጉጉት አድሮበት  የነበረው የውስጥ አርበኛው ሸሪፍ እስከነአካቴው በሰው አገር ለመኖር ተገደደ።የአባቱን በጦርነት መሞት ከብዙ ዓመት በኋላ  መርዶ ደረሰው።ይሰራበት የነበረው ግብጻዊም ሞተ።ሸሪፍ ለመኖር የነበረው ምርጫ በሾፌርነት ሞያ መቀጠልና የከፍተኛ የጭነት መኪና መንጃ ፈቃድ አውጥቶ መስራት ነበር፤ያም ፍላጎቱ ሰመረለትና የጭነት መኪና ይዞ እየዘወረ የሱዳንን መሬት ከዳር እከዳር እየሰነጠቀ የሚጓዝ ጠንካራና ደፋር ሾፌር ሆነ።በሙያው ብቻ ሳይሆን ሸሪፍ ኢትዮጵያ አገሩን የሚወድና ኢትዮጵያውያንን የሚረዳ ፣እርቄአለሁ ብሎ የማይርቅ፣በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምንና የሚኮራ፣በዓመት በዓላት ቀናት አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ጥለት ያለውን ነጠላ አጣፍቶ ቤተክርስቲያን ተሳልሞ ኢትዮጵያውያንን ሰብስቦ የሚያበላ፣የሚመክር ትልቅ ምሳሌ የነበረ፣በልጅነት ተሰዶ በአዛውነንትነት በሰው አገር አፈር የለበሰ፣ የወለጋ ተወላጅ፣የኦሮሞ ብሔረሰብ አባል የሆነ ኢትዮጵያዊ ነበር።ታሪኩን ከራሱ ከባለቤቱ የሰማሁት ሲሆን ለአሁኑ ትውልድ ትልቅ ትምህርት እንደሚሰጥ በማመን ለመጻፍ ተገድጃለሁ።ኦሮሞ ለአገሩ ለኢትዮጵያ ደሙን ያፈሰሰ ዜጋ እንጂ ተለይቶ የኖረ ባዳ ሕዝብ አለመሆኑን በውስጥ አርበኛው  በሸሪፍና ለኢትዮጵያ አገሩ ነጻነትና ክብር ደሙን ባፈሰሰው በአርበኛው አባቱ በአባ ጃክሶ ታሪክ ልንደሰትና ልንታደስ ይገባል።

አገሬ አዲስ